# የፌዴሬሽንና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በሮም ከሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተካሄደ

በፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ካሳ ተክለብርሃን የሚመራ የህዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ቡድን በጄኔቭ የፓርላመንታሪ ህብረት ስብሰባ ተሳትፎ ወደ አገር ቤት ለመመለስ በሮም ትራንዚት ባደረገበት ወቅት ሮም ለሚገኙ የዲያስፖራ አባላት በአገር ቤት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ወዘተ ጉዳዮች ዙሪያ እየተከናወኑ ስላሉ ሥራዎች መረጃ ለመስጠትና ዲያስፖራው የሚያነሳቸውን የተለያዩ ሃሳቦች በመስማት ለመወያየት መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም. 120 የሚሆኑ የዲስያስፖራ አባላት በተገኙበት ውይይት ተካሂዷል::



ውይይቱ በክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ መሪነት የተካሄደ ሲሆን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ካሳ ተክለብርሃን በአገራችን በማንኛውም ጊዜ የማይናወጥና በየጊዜውም እየተጠናከረ የሚሄድ የሰላምና የዲሞክራሲ ሥርዓት የመገንባት ሥራ ማከናወን በአምስት አመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት እንደሚገኝ፣ ለዚህም በህገ መንግስታችን የተቀመጡ የዲሞክራሲ ሥርዓቱን ለመገንባት መሠረታዊ የሆኑትን ህዝብን የማሳተፍና የዲሞክራሲ

ተቋማትን የመገንባት ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን፤ ይህም ቀጣይነት ያለውን የኢኮኖሚ እድገት በማረጋገጥ የህዝቡን ኑሮ ለመለወጥ ከፍተኛ ሚና እንዳለውና በአጠቃላይ በእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ እቅድ መሠረት በትምህርት፣ በጤና፣ በመሠረተ-ልማት፣ በግብርና እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ የተሰሩና እየተሰሩ የሚገኙ የልማት ስራዎችን፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን በተመለከተ ገለጻ ሰጥተዋል፡፡



በመቀጠልም መድረኩ ለስብሰባው ተሰታፊዎች ጥያቄና ለአስተያየት ክፍት የተደረገ ሲሆን በፍትህ አካላት አካባቢ የሚገኙ የባለሙያዎች አቅም ከመገንባት አኳያ በመንግስት እየተወሰደ ስላለ እርምጃ፣ በተለያዩ አደረጃጀቶች ለታቀፉ የዲያስፖራ አባላት በመንግስት ሊሰጥ ስለሚችል ድጋፍ፣ ቡናን በጥሬ ከመላክ ይልቅ አሽጐ በመሸጥ የተሻለ ገቢ ለማስገኘት እየተከናወነ ስላለ ስራ፣ ቀደም ሲል በአገራቸው የመኖሪያ ቤት መገንባት እንዲችሉ መሬት ከመንግስት ተረክበው ግንባታ የጀመሩ የቤት ሥራ ማህበራት ግንባታውን ለመቀጠል የሚያስፈልገው የግንባታ እድሳት ፈቃድ በማግኘት ስላጋጠማቸው ችግር፣ ለአንድ አገር እድገት ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ከመሆኑ አኳያ ልማት ለቴክኖሎጂ በመንግስት በኩል ትኩረት ተሰጥቶት እየተደረገ ስላለ እንቅስቃሴ፣ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የዲያስፖራ አባላት ወደ አገር ቤት በሚገቡበት ጊዜ የሚያጋጥማቸው የቢሮክራሲው እርስ በርስ ያለመናበብ ችግር ስለሚፈታበት ሁኔታ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ የተሰጠባቸው ሲሆን በአጠቃላይ በተነሱት ጉዳዮች ላይ በተደረገው ውይይት የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ስብሰባው ተጠናቋል፡፡